የሰ/መ/ቁ 107487

ሐምሌ 8/2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

**አመልካቾች፡-** 1ኛ. ብርሃኑ ዲባባ

2ኛ. አለሚቱ ዲባባ

3ኛ. ተካ ዲባባ

4ኛ. አበበ ዲባባ } አልቀረቡም

5ኛ. መሰረት ዲባባ

6ኛ. ዘነበች ዲባባ

7ኛ. አሸናፊ ዲባባ

8ኛ. አፀደ ዲባባ

**ተጠሪ፡-** የለም

መዝገቡን መርመረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የሚመለከተው ለወራሾች የሚሰጥን የምስክር ወረቀት ነው፡፡ የአሁን አመልካቾች ለወልመራ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ አቶ ዲባባ ሁሪሳ ስለሞቱ ወራሽ መሆናቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ ከአቤቱታቸው ጋር ተያይዞ የውርስ አጣሪዎች ሪፖርት ቀርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም አመልካቾች የሟች ልጆች በመጀመሪያ ደረጃ የሟች ወራሾች መሆናቸውን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 842 እና የውርስ አጣሪ በ20/09/2006 ዓ.ም የተፃፈ ሪፖርት ወራሾች ለመሆን ያቀረቡትን በማረጋገጥ በፍ/ብ/ህ/ቁ 996 መሰረት የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው ወስኗል፡፡ ነገር ግን አመልካቾች የወራሽነት ማስረጃውን ለማስረጃነት ከፈለጉ የብር 60,000.00 /ስድሳ ሺ ብር/ ዋስትና ለ3 አመታት ታግዶ የሚቆይ ሊያቀርቡ ይገባል በማለት ትዕዛዝ አስተላልፏል፡፡

አመልካቾች የተጠየቀውን ዋስትና በመቃወም ለፊንፊኔ ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ እና ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በሰበር ቅሬታቸውን ያቀረቡ ቢሆንም እንደቅደም ተከተሉ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የለበትም እንዲሁም መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ ቅሬታቸው ውድቅ ተደርጓል፡፡

የሰበር አቤቱታ ለዚህ ፍ/ቤት የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ታህሳስ 2/2007 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የአባታችንን ንብረት የነበረውን በሕጉ መሰረት አግባበ ባለው ሁኔታ አጣርተን ድርሻ ድርሻችንን ካወቅን በኋላ ፍ/ቤቱም ወራሽነታችንን ተቀብሎ ማስረጃ እንዲሰጠን ባቀረብነው ጥያቄ መሰረት ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ ማስታወቂያ ወጥቶ ንብረቱ ላይና በተለያየ ቦታ ተለጥፎ ለብዙ ጊዜ የቆየ ቢሆንም ተቃዋሚ አለመቅረቡን ፍ/ቤቱ አረጋግጦ ወራሽ መሆናችንን የተቀበለ ሲሆን ምንም ጥርጣሬ በሌለበት ሁኔታ የግድ ዋስትና ብር ካላስያዙ ማለቱ መብታችንን የሚገድብ በመሆኑ እና ሕጉም የወራሽነት ማስረጃ ለመውሰድ ገንዘብ ማስያዝ እንዳለብን በግልፅ የሚደነግግ ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ያሳለፉት አላስፈላጊ ትዕዛዝ ይሻርልን ብለዋል፡፡

የአመልካቾች ቅሬታ ተመርምሮ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ዋስትና ያስይዙ የመባሉን አግባብነት ለማጣራት ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

በበኩላችን አመልካቾች ያቀረቡትን ቅሬታ፤ አቤቱታ ከቀረበበት ትዕዛዝ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርመረናል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ የሟች ልጆች በመጀመሪያ ደረጃ የሟች ወራሾች በመሆናቸውና ውርሱም ስለተጣራ ፍ/ቤቱ ወራሽ መሆናቸውን እና የውርሱን ሀብት የሚያመለክት የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው የጠየቁበት ነው፡፡ ማስረጃ የጠየቁት ወራሾች እና የውርሱ ሃብት ተጣርቷል ተብሎ በክስ ማመልከቻው ላይ ተዘርዝሮ ስለመቅረቡ የስር ፍ/ቤት ይሰጥ ባለው የወራሽነት ማስረጃ ላይ ተመልክቷል፡፡ በወራሾች እና በውርሱ ሀብት ላይ የቀረበውን የምስክር ወረቀት ጥያቄ የስር ፍ/ቤት ተቀብሎ ይህ ነው የሚባል ምክንያት ሳይሰጥ አመልካቾች የወራሽነት ማስረጃውን ከፈለጉ የብር 60,000.00 ዋስትና ለ3 አመት ታግዶ የሚቆይ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 996/2/ እንደተመለከተው የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጡ ጥያቄ የቀረበላቸው ዳኞች ጥያቄ ያቀረበው ወራሽ ማስረጃዎቹን ሁሉ እንዲያቀርብና አሰፈላጊ መስሎ የታያቸውን ማናቸውንም የማረጋገጫ ዋሰትና እንዲሰጣቸው ሊያስገድዱት ይችላሉ፡፡

ከተጠቀሰው ሕግ መረዳት እንደሚቻለው የወራሽነት የምሰክር ወረቀቱን ለመስጠት የማረጋገጫ ዋሰትና እንዲሰጥ የሚደረገው አሰፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ስለሆነም ፍ/ቤቱ ዋሰትናውን የሚጠይቅበትን ምክንያት ገልፆ ዋስትና እንዲሰጥ ከሚያስገድድ በቀር ይህ ነው የሚባል ዋስትና የሚያሰጠይቅ ምክንያት ስለመኖሩ ሳይገለፅ ዋሰትና እንዲሰጥ ማስገደዱ ሕጉን ያልተከተለ እና የማስረጃ ጠያቂውን መብት የሚጋፋ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የስር ፍ/ቤት ምክንያቱን ሳይገልፅ አመልካቾች የወራሽነት ማስረጃውን ከፈለጉ የማረጋገጫ ዋስትና ያቅርቡ በማለት ያሳለፈው ትዕዛዝ እና ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር የተመለከቱ ፍ/ቤቶችም ትዕዛዙን ሳያርሙ ማለፋቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የወልመራ ወረዳ ፍ/ቤት ቡራዩ ችሎት በመ/ቁጥር 48667 በ30/10/2006 ዓ.ም፤ የፊንፊኔ ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 23005 ነሐሴ 2/2006 ዓ.ም እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 187713 ህዳር 9/2007 ዓ.ም ያሳለፉት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካቾች የሟች አባታቸው አቶ ዲባባ ሁሪሳ ወራሾች መሆናቸው ስለተረጋገጠ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 996 መሰረት የወራሽነት ማስረጃ ይሰጣቸው በሚል የተላለፈው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. አመልካቾች የወራሽነት ማስረጃውን በማስረጃነት ከፈለጉ ለ3 አመታት ታግዶ የሚቆይ የብር 60,000.00 ዋስትና ያቅርቡ በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
4. የወልመራ ወረዳ ፍ/ቤት ቡራዩ ችሎት ስለዋስትና ያሳለፈው ውሳኔ መሻሩን አውቆ የወራሽነት ማስረጃውን ለአመልካቾች ይስጥ፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ